# ማን ያውራ የነበረ 7

ዋናው ቁምነገር ጉዞው እንጂ  መዳረሻው ወይም መጨረሻው አይደለም የሚሉ አሉ፡፡ የሕዝብን ትግል በተመለከተ ግን፥ ከየት ተነስቶ የት ለመድረስ፤ በማንና በምን ላይ ድል ተቀዳጅቶ ምንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽን ይጠይቃሉ፡፡ ድርጅቶች ፕሮግራም የሚያስፈልጋቸው ለዚሁ ነው፡፡ ይህ ነው ዓላማችን፤ምኞታችንና ግባችን ብለው፥ ለሕዝብ ለማቅረብና የሕዝብንም ድጋፍ ለማግኘት ማለት ነው፡፡ ፕሮግራም ሲሉና ፕሮግራም ስንል ከባድ ልዩነት እንዳለና እንደነበረም ማሳየቱ ተገቢ ነውና  ኢሕአፓና የፖለቲካ ፕርግራም ጥያቄ የሚለውን ማቅረብ እንፈልጋለን፡፡

በአሁኑ ጊዜ ፖለቲካም ትርጉም አጥቶ፤ትግልም ከሞላ ጎደል ቧልት ሆኖ የሚታያቸው በበዙበት ወቅት፥ ለድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም የሚሰጠው ትርጉም የቀለለ ቢሆን ከቶም አያስገርምም፡፡ በስድሳዎቹ ዓመታት የድርጅት ፕሮግራም ፅፎ የሚሸጥ የባዕድ ጠበቃ ነበርና ቢያንስ በወቅቱ ነፃ አውጪ ነኝ ይል የነበረ አንድ ድርጅት፥ በዚሁ ባዕድ ፕሮግራም አፅፎ ገዝቶ ማሰራጨቱን እናስታውሳለን፡፡ ወያኔ ትላንትም ዛሬም ከልሳኑ እስከ ውጭ ጉዳይ ፕሮግራሙ ባዕዳንን ቀጥሮ ተልሙት፤ፃፉት አከናውኑት እያለ ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ ፕሮግራማቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ጋር ይገናኝ አይገናኝ ብዙም ሳይጨነቁ ኃያሉ መንግሰት መን ደስ ይለዋል፤ምዕራባውያን ለጋሾች ምን ያስደስታቸዋል ብለው በመነሳት ለባዕዳኑ ፕሮግራም ያረቅቃሉ፡፡ ሰነፍ ያሉት ደግሞ ትንሽ የቃላት ለውጥ ያደርጉና የሌቅችን ፕሮግራም አድሰው (ፍራሽ አዳሽ-ፕሮግራም አዳሽ) ዓይናቸውን ሳያሹ የእኛ ብለው ያሰራጫሉ፡፡ ዛሬ ፕሮግራሞች ቢመሳሳሉ ሁሌም ዓላማ ተመሳስሎ ሳይሆን፥ ግልበጣና ኩረጃውም ተፋፍሞ ነው፡፡ ለዚህም ነው ድርጅቶች፥ ሥራቸው ሆነ ለራሮቸው የሚሰጡት ርዕዩተዓላማዊ ገለፃ አልጣጣም የሚለው፡፡ ወያኔ ለምሳሌ በኤኮኖሚው ላይ ለሙሉ ትንሽ ጎደል ቁጥጥሩን አስፍኖ፥ የለም የነፃ ገበያ  አባወራ ነኝ የሚለው፡፡ ሌሎች ደግሞ ቆምንለተ ያኩተ ስርዓት ራሱ ምን ማለት እንደሆነና ለሀገርም ምንን እንደሚያስከትል ግልፅነትና ግንዛቤ ጎድሏቸው በደፈናው ዴሞክራሲ በሚለው ሽፋን ተጠቅልለው ሊደበቁ የሚፈልጉት፡፡

ለኢሕአፓ ፕሮግራም የቃል ጨዋታ ወይም የማያምንበትንና በስራ የማያውለውን አሳምሮ መደርደርያ ሆኖበት አያውቅም፡፡ የድርጅቱን ፕሮግራም መቀበል መደገፍ ወይም አለመቀበል፥ መቃወም የዜግነት  መብት ቢሆንም፥ ድርጅቱ ፕሮግራሙን ያወጣውና እያወጣ ያለው በፖለቲካ ራዕዩ ወይም ርዕዮቱ መትረት ነው፡፡ ኢሕአፓን የወለደው ተራማጅ እንቅስቃሴ ግራ ክንፍ ዝንባሌ የነበረውና ለስር ነቀልም ለውጥ የቆመ ስለነበር፥ የኢሕአፓም የወቅቱ ፕሮግራም ነጥቦች የዚሁ ነፀብራቆች ነበሩ፡፡ በዴሞክራሲ፤በመሬት፤በብሄረሰብ፤በኤኮኖሚ ወዘተ ጥያቄዎች ይህ ዝ ባሌውም ተንፀባርቋል፡፡ ከዝርዝር ፕሮግራም ነጥቦች ውስጥ ግን መሰረታዊ ወይም ማገርና ምሰሶ የሆኑ ክቡር መርሆችና አቅዋሞቹ ሳይቀየሩ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች መሰረታዊ መርህና  የፕሮግራም ነጥብ ስለተደባለቀባቸው ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ለመግጠም ሲሉ፥ ፕሮግራም ሲቀይሩ በዚያውም መርሆአቻውን ይጥላሉ፡፡ ይህ ከኢሕአፓ አቅዋም ጋር የማይጣጣም ነው፡፡ ኢሕአፓ በመሰረታዊ መረህ ደረጃ ይዞት የተነሳውና እስከዛሬም ፀንቶና አንዳንዶች  እንደሚሉት “ድርቅ” ብሎ የቀጠለበት ሕዝባዊ መርህ አለ ፡፡ ይህም የፖለቲካ ስሥልጣን ለሕዝብ መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ ሕዝባዊ ሬፑብሊክ ተባለ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን ወሳኝ፤ የሥልጣን መንጭ የሕዝብ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ይህ መሰረታዊ አቋም በየፕሮግራሞቹ ተንፀባርቋል፤ የፕሮግራሙን ይዘትም ቀርጿል፤ቃኝቷል፡፡ ይህ በመሆኑም ምርጦች ነን፤የሕዝብ ሞግዚት ነን፤ ለሕዝብ የምናውቅለት እኛ ነን ወዘተ ብለው ብቅ ካሉ ኃይሎች ጋር ሁሉ ኢሕአፓ ተጋፍጧል፡፡ ዛሬም የወያኔን ዘረኛ ቡድንና በዴሞክራሲ ስም የምርጦች መንግስት ሊመሰርቱ የሚሹትን በየፈርጃቸው የሚታገላቸው ለዚህ ነው፡፡ ዴሞክራሲን ሊገድቡ፤ሕዝብን የበይ ተመልካች፤ተለጣፊና አጫፋሪ ሊያደርጉ የተነሱተን ሁሉ የሚታገላቸው ለዚህ ነው፡፡ የስርዓቱ አወቃቀርና ቅርፅ ይህ ሆነ ያ፥ በመሰረቱ ወሳኙ ሰልጣን የሕዝብ መሆን አለበት ሲለ ኢሕአፓ ያምናል፡፡ ይህም በትላንትም ሆነ በዛሬ ፕሮግራሙ በገሀድ የሚንፀባረቅና የሚያምንበትም ነው፡፡ የእምነት ጉዳይ ባልነበረማ ደጋግመን እንዳልነው ኑ ተሾሙ፤ ከፍርፋሪው ይድረሳችሁ ላለ ገዢ ተብዬዎች ሁሉ ኢሕአፓ ራሱን ለሽያጭ ባቀረበ ነበር፡፡

ሌላው በኢሕአፓ ፕሮግራም ሁሌም አለሁ ያለና የሚል ክቡር መርሆ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና አንድነት የሚመለከት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ባዕዳን አይደፈር ሲልና የባዕድ ጦር ሰፈር ይነቀል ብሎ ገና ከምስረታው ሲታገል የያዘው ፍፁም ኢትዮጵያዊ አቋም ላይ ገዢዎች ቢዘምቱም ህቁን ከቶም መቀየር አልቻሉም፡፡ የአፄው መንግስት ራሱን ለአሜሪካ ሸጦ እያለ የታገሉትን ተማሪዎች የሶቭየት ቅጥረኞች ብሎ ሊያጥላላ ሞክሮ ነበር፡፡ ደርግም በበኩሉ ራሱንና ሀገሪቷን ለሶቭየት-ለሩሰያ ሸጦ እያለ ኢሕአፓን የሲአይኤና የአረብ ቅጥረኛ ብሎ ሲወነጅል ነበር፡፡ አልፎም የዚያድ ባሬና የሶማሊያ ደጋፊ ብሎ በሀሰት ኢሕአፓ ላይ የነዛው ዘመቻ ይኸው እስከዛሬ ሀገርን ክደው ከርመው በነበሩ አስመሳይ ሀገረ ወዳዶች እየተሰራጨ ነው፡፡ ኢሕአፓ የብሄር ብሄረሰብ መብት ብሎ የወሰደው አቋም  በነበረው የጊዜው ርዕዮት የተቃኘ ቢሆንም የሀርን አንድነት በሕዝብ ፈቃደኝነት ላይ መመሰረት ይገባል ብሎ አምኖ የወሰደው አቅዋም ነበር እንጂ ዛሬ አንዳንድ ትምክህተኞች ሆኑ ጠባቦች እንደሚሉት ሀገሪቷ ትፍረስ ትበጣጠስ ብሎ አልነበረም፡፡ ትፍረስ ብሎ በነበረማ ተባብረን እናፍርሳት ካሉ ወያኔያውያን ሆኑ ባዕዳን ጋር ባበረ ነበር፡፡መሳሪያም ገንዘብም ሙሉ ድጋፍንም አግኝቶ ለስልጣን በበቃም ነበር፡፡ ለዚያድ ባሬና የሶማሊያ ወረራ ድጋፍ ሰጥቶ በነበረማ፥ እንደ  ወያኔና እንደነ  ደረጀ  ደሬሳ  ኢፒዲኤ-ኢዴኃኅ በሞቃዲሾ ቢሮ ከፍቶ፤ በሶማሊያም ተደግፎ በተገኘ ነበር፡፡ እንደ ወያኔ ግማሽ የኢትዮጵያ ግዛት የሶማሊያ መሬት ነው ብሎ ቢፈርም ቢፈጠም ኖሮ፥ እውነትም የሶማሊያንም የአረቡንም ድጋፍ ባገኘ ነበር፡፡ ዛሬ የኢሕአፓን ኢትዮጵያዊ አቋም በጥያቄ ሊያስገቡ የሚሞክሩት ትላንት የሀገርን ሉዓላዊነት ለሸጠ ሥርዓት ሲያገለገሉ የነበሩ፤ለባዕድ ኃይል በሎሌነት የተሰለፉና ሀገር ኡ ኡ ስትልና የኢሕአፓ አባላትና ሕዝብ ጩኸቷን ሰምተው ሲሰዉላት እነሱ ግን የግል ኑሯቸውን ሲያበጃጁ የነበሩት ናቸው፡፡ ስለዚህም ዛሬም ቢሆን ወያኔ የሸፋን ሰሙን ኢሕአዴግ ብሎ ኢትዮጵያዊ የሚለውንም ቢጨምርም፤ ትላንት ሕዝብን ሲመትሩና ሲፈጁ ቆይተው ዛሬም በፀረ ሕዝብ ከፋፋይ ተልዕኮ ተሰማርተው ራሳቸውን የኢትዮጵያዊነት ካባ ቢያለብሱም፤ ፕሮግራም ባሉትም ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ብለው ቢያሰፍሩም፥ በስራቸውና በሚያምኑት ደረጃ ግን ይችን ሀገር አስቀድመዋል ማለት ከቶም አይቻልም፡፡ ዛሬም በሀይማኖትና በብሄረሰብ ልዩነት ያምናሉ--ስለዚህም በተጨባጭ ፀረ አንድነት ናቸው፡፡ ኢሕአፓ የብሄረሰብ እኩልነትና ዴሞክራሲ የአንድነት መሰረት መሆን አለበት ባይ ነውና፤ የነበረውን ሆነ ያለውን ዘረኝነትና የብሄረሰብ ጭቆና የሚክድ አይደለምና ከእነሱ የተለየ ነው፡፡ ለኢሕአፓ ኢትዮጵያና ሕዝቧ የትግሉ አልፋ ኦሜጋ ናቸው፡፡ የፕሮግራሙም እንዲሁ፡፡ በአጭሩ የኢሕአፓን  ኢትዮጵያዊነት በጥያቄ ለማስገባት መዳዳት ከባድ ስህተት ነው ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡

ለኢሕአፓ ዝርዝር የፖለቲካ ፕሮግራም የመሠረታዊ አቋምና መርህ ተቀጥላ ነው፡፡ ሁኔታዎች ሲለወጡ ፕሮግራም ይቀየራል፥ ግን ለሀገረና ለሕዝበ የተገባ ቃል ኪዳን ይታጠፋል ማለት አይደለም፡፡ ኢሕአፓ በትግሉ ሂደት ከሕዝብ እየተዋሀደና የሀገሩን ሁኔታም በሚገባ እያወቀ ሲሄድ፥ የተሳሳቱ አቋሞቹን አስተካክሏል፤አርሟል፡፡ አጠፋሁ ማለትም አልከበደውም፡፡ ትላንት ለአረመኔ ሥርዓት አድረው ደም ያፈሰሱ ግን ዛሬም አጠፋን ማለት አቅቷቸው ማየታችን ግን መጠቀስ ያለበት ነው፡፡ በዝርዝር ፕሮግራም ደረጃ ኢሕአፓ በመሬት ጥያቄ፤ በማገር ጥያቄ ወዘተ ለውጦችን አድርጓል፡፡  የለውጦቹ መሠረት ግን፥ አሁንም  የሕዝብን ጥቅም የሚያስቀድም ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ኢሕአፓ ፕሮግራሜ ፍፁምና አማራጭ የለሽ ፍቱን መድሀኒት ነው በሚል መንፈስ ግብዝ ሆኖ ያቀረበው ሳይሆን፥  ይበጃል በሎ ለሕዝብ ግምገማና ፍርድ የሚተወው ነው፡፡  ዕምነቱ ስለሆነ ለዚሁ ይታገላል፡፡ ግን ዕምነቱን በሕዝብ ላይ መጫን አለብኝ ባይ ስላልሆነ ደግሞ፥ ዛሬም እንደ ትላንት ወሳኙ ሕዝብ ነው ሲል ኢሕአፓ ያምናል፡፡ ፕሮግራም ሲሉ የይስሙላ ወይም የቅጂ ሰነድ ከሆነባቸው ኢሕአፓ ይለያል፡፡ አቋሙን ከተግባሩ ተቀናጅቶ  ቢመረመር ፕሮግራም ሲል ለይስሙላ ሳይሆን፥ ላመነበት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ለሕዝበ  ይህ ነው ዕምነታችን ካልን ደግሞ ቃላችን ማክበር የሚጠበቅ ነው፡፡ ኢሕአፓ ደግሞ ቃል ኪዳኑን ፀንቶ ማክበር የቆየ መለያው ነው፡፡